# ድርድር ረግጦ መውጣት እንደፖለቲካ ግብ...

ታደገ ከካዛንቺስ 10/30/09

በአለማችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ህልውናና የዚህ ስርዓት መገለጫ የሆነው ስልጣንን በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መያዝ ከተጀመረ ምዕተ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ በኢትዮጵያ የምርጫ ታሪክ አጭር ቢሆንም ከመጀመሪያው፣ ሁለተኛው ከዚያም ሦስተኛው ዙር የተካሄደው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ የሕዝቡ ተሳትፎና የምርጫው ሂደት ዴሞክራሲያዊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ በአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ምን ያህል እየጎለበተ እንደመጣ አመላካች ነው፡፡

እስካሁን ባካሄድናቸው ሦስት ክልላዊና አገራዊ  ምርጫዎች ህዝቡ ይሠሩልኛል የሚላቸውን ተወካዮቹን በነፃ መንፈስ መምረጥ እንደሚችል ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ፓርቲን ወክለውም ሆነ በግል ተወዳድረው የሚመረጡት ተወካዮች በፓርላማ ውስጥ ያለአንዳች መሸማቀቅና ተፅዕኖ ያመኑበትን በመደገፍ  ያላመኑበትን ደግሞ በግልፅ በመቃወም ወክለነዋል የሚሉትን የህብረተሰብ ክፍል ድምፅ በነፃነት አንፀባርቀዋል፡፡

ህበረተሰቡም ከምርጫ ኮሮጆ የሚገኝ ድምጽ አገር ማስተዳደር አቅም እንዳለው በመረዳቱ "ድምጽ ቢሰጥ ባልሰጥ ለውጥ አላመጣም" የሚለውን የተሳሳተ አባባል ውድቅ በማድረግ በነቂስ ወጥቶ ድምጽ እየሰጠ ይገኛል፡፡  እናም በአሁኑ ወቅት በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን ተፈጥረው አማራጭ ኃሳብ አለኝ የሚሉትን በማቅረብ የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ደፋ ቀና የሚሉ የመኖራቸውን ያህል ስልጣን መያዝ የሚቻለው በሠላማዊና ህጋዊ መንገድ ሳይሆን በኃይልና ፀረ - ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነው ብለው እንቅስቃሴ የጀመሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም አልጠፉ፡፡ ታዲያ የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት ተዘንግቶ ያረጀ ያፈጀ ፖለቲካ ማራመድ ለዚች አገር ዕድገት ምን ሊፈይድ ይችላል? በዚህ የስልጣኔ  ዘመን እንዲህ ያለው ተራ አስተሳሰብ ውጤት ሊመጣ ይችላልን?  ሁሉም ሊያስብበትና አንድ ምላሽ ሊሠጥበት የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ይታየኛል፡፡

ይህን ጉዳይ ላነሳ የቻልኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ አሁንም በአዜውና በአምባገነን ሥርዓት ውስጥ ይደረግ እንደነበረው ምርጫ የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት የዘነጉ አንዳንዱን የፖለቲካ ድርጅቶች ማየት በመጀመራችን እንጂ፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለኝ በአሁኑ ሠአት በተቃውሞ ጐራ የተሠለፉት አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ከበፊት ስህተታቸው ሳይታረሙ በመጪው ምርጫ ልንሳተፍ እንችላለን አሊያም ደግሞ ሌላ የስልጣን ማግኛ አማራጭ እንዘይዳለን በማለት ቅስቀሳ ሲያደርጉ በማየቴ ነው፡፡ ልብ ብሎ ለተመለከተው ይህ የሥልጣን ሽኩቻ ለህዝብ ጥቅም ሳይሆን  የግል ጥቅምን ለማሳደድ አሊያም ለምርጫ በቂ ዝግጅት ካለማድረግ የተነሳ ከህዝብ ድምፅ ውጪ ስልጣን ለመያዝ ዘዴ መቀየስን የሚያመላክት ነው፡፡

በአገራችን ኢትዮጵያ የሠለጠነ የፖለቲካ ትግል ሚስጥሩ የገባቸው የፖለቲካ ስብስቦች ቢኖሩም ቀኑ ጨለማ የሆነባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች/ስብስቦች / ዛሬም ድረስ መታየታቸው በጣም ያስገርማል፡፡ በሠለጠነ የፖለቲካ ትግል ያመኑት አገሪቱን እያስተዳደረ ካለው ገዥ ፓርቲ ጋር ወሳኝ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይትና ድርድር በማድረግ ቀጣይ የትግል ስልታቸውን አመቻችተዋል፡፡ በሠላማዊና በሠለጠነ የፖለቲካ ትግል የማያምኑት በምርጫ ሥነ ምግባር ዙሪያ የሚደረገውን ድርድር ረግጦ በመውጣት የመጪውን ምርጫ ሂደት  ለማጨለም ወገባቸውን ማጠባበቁን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ አገራችን የተያያዘችውን የዴሞክራሲ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ሆን ተብሎ የተሴሬ ደባ እነደሆነ በግልጽ ያሳያል፡፡

የድርድርንና ውይይትን ጠቀሜታ በመረዳት ከነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ ሲካሔድ የነበረው የተቃዋሚ ፓርቲዎችና የገዥው ፓርቲ ድርድር ሠላማዊ በሆነ መንገድ መጠናቀቁን በሚዲያ ስሰማ የመድረክ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ትንሽ ነገር ጫረብኝ፡፡ ምክንያቱም ወሳኝ በሆነ አገራዊ አጀንዳ ላይ ውይይት ማድረግ አለመቻሉ ወደፊት ምን አይነት የትግል ስልት ቀይሶ እንደሆነ መገመት አያዳግትምና፡፡

በፓርቲዎች መካከል የተካሄደው ድርድር በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት በተደጋጋሚ በሚዲያ ሲገለፅ ሰምቻለሁ፡፡ በዋናነት በምርጫ ወቅት ሊነሱ የሚችሉ አላስፈላጊ ግጭቶችን ለማስወገድ ፣ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫን ለማበረታታትና የመብት ጥሰቶችን እንዳይከሰቱ ለመከላከል የሚያግዝ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ እስቲ ሰለውይይቱ ካነሳሁ አይቀር የውይይቱ ገጽታ ምን ይመስላል? የሚለውን ትንሽ ላንሳላችሁ፡፡ በዚህ ድርድር መጀመሪያ ላይ መድረክ፣ ኢዴፓ፣ መኢአድ፣ ቅንጅትና ኢህአዴግ ቢሰተፋም ስንካላ ምክንያት በማቅረብ ‹‹መድረክ›› የተባለው የተቃዋሚ ፓርቲ ስብስብ ድርድሩን ረግጦ መውጣቱን ይታወሳል፡፡

ይሁንና በድርድሩ የመጀመሪያ ምዕራፍ እስከመጨረሻው የዘለቁት ፓርቲዎች (ኢህአዴግ፣ ኢዴፓ፣ መኢአድና ቅንጅት) ውጤታማ የሆነ ድርድርን በማድረግ ስምምነት ላይ በመድረስ የድርድሩን የመጀመሪያ ምዕራፍ ማጠናቀቃቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህም ፓርቲዎች ስምምነታቸውን በፊርማ ለማጽደቅ በዝግጅት ላይ እንደሆኑ ይገለፃል፡፡ ድርድሩን የሚከታተሉ ምንጮች እንደሚገልፁት ከሆነ ለሁለት ወራት ያህል ሲካሔድ የቆየው ድርድር "የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ - ምግባር ደንብ" እና "የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ የማስፈፀሚያ ስልቶች" የሚሉ ሁለት ሰነዶች ላይ ነበር፡፡

ድርድሩ በእኩልነት መንፈስና በሠጥቶ መቀበል መርህ ላይ በመመስረት የተከናወነ፣ የተሳተፉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሉባልታንና የርካሽ እወደድ ባይነት ፖለቲካን ይቅርብኝ በማለት ሰላማዊ መንገድን መርጠው ለሕግ ተገዥነታቸውን በሰከነ መንፈስ ያረጋገጡበት ነበር፡፡ ገዥው ፓርቲም የድርድሩን አስፈላጊነት በግልጽ በመረዳት ጊዜውን ለዚሁ ዓላማ በትኩረት ማሳለፉ የሀገሪቱን ፖለቲካ ለዘመናት ታፍኖ ከቆየበት ፍጥጫ ወደ ሰከነና ሠላማዊ የድርድርና የውይይት ፖለቲካ ያሻጋገረ ሂደት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህ አይነት የሰከነ፣ የሠለጠነና ሠላማዊ ውይይትና ድርድር በመብቃታችንም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አለን፡፡ የትግል ስልቱ የጠፋባቸውንና አመፅ አመፅ ያሰኛቸውን ደግሞ ልቦና እንዲሠጣቸውና ወደ ድርድሩ እንዲመለሱ ሲንል እንፀልያለን፡፡

ወደዋናው ቁም ነገሬ ልመለስና በዚህ ወሳኝ የሆነ ድርድር ላይ ያልተሣተፈው የሁለት ግለሠቦችና የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው ‹‹መድረክ›› የተባለው ፓርቲ ምን አይነት የፖለቲካ ስልት ቀይሶ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ መድረክ በድርድሩ መሳተፍ የምፈልገው ከገዥው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው የሚል ሃሳብ ማምጣቱ ተልካሻ ምክንያት መሆኑን በተለያዩ ሚድያዎች ሲገለፅ ቆይቷል፡፡ እርግጥ ነው አገራዊ አጀንዳዎች ላይ ሁሉም ህጋዊ ፓርቲዎች ባሉበት ቢካሄድ ምን ክፉት አለው? ‹‹ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገንቢ ሐሳብ ሊያቀርቡ አይችሉም፣ የእኔን አቋም ከማይደግፍ ተቃዋሚ ስብስብ ጋር ውይይት ማድረግ አልሻም ወዘተ›› የሚሉትን ምክንያቶች መደርደር ምን የሚሉት ተረት ነው?

እስኪ የአሜሪካኖቹን የዴሞክራትና የሪፐብሊካን ፓርቲዎችን ሁኔታ ትንሽ ላስታውሳችሁ፡፡ የሂላሪ ክሊንተን ፓርቲና የባራክ ሁሴን ኦባማን ፓርቲ በምርጫ ወቅት ሲያደርጉት የነበረውን የምርጫ ቅስቀሳ ስንመለከት፤ ሠላማዊና የተዋጣለት ቅስቀሳ ነበር፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን ሠላማዊ ቅስቀሣው ሳይሆን ከምርጫ ውጤት በኋላ በአብላጫ ድምፅ ያሸነፈው በኦባማ የሚመራው የዴሞክራት ፓርቲ ስልጣኑን ተቀናቃኝ ለነበራችው ሂላሪም አልነፈጋት፡፡ እዩ እንግዲህ ምን አይነት የህዝብ አስተዳደር ላይ እንደደረሡ፡፡ እኛ አገር ግን ስልጣን ላይ ለመውጣት መሯሯጥ እንጂ ለህዝብ አስተዳደር የሚነሡ ተቃዋሚዎችን ማየት አልቻልንም፡፡ መድረክ የሚባለው ፓርቲም ገና ከወዲሁ ድርድርን መርገጥ ጀምሯል፤፡ እንኳንስ በውድድር ሜዳ ገብቶ ልክ የአሜሪካን ተሞክሮ ሊያሳየን ይቅርና በተቃዋሚ ጐራ የተሠለፉትን ፓርቲዎች የማዳመጥና ከእነርሱም ጋር የመወያየት ትዕግስቱ የለውም፡፡

በመጪው 2002 አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ኢህአዴግን አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ በርካታ ፓርቲዎችን ያሰባሰበው መድረክ መጀመሪያውኑ ስብስቡ የሚያዛልቀው አይመስለኝም፡፡ በመድረክ ጥላ ስር የተሠባሠቡት ፓርቲዎች በቁጥር ስምንት ይሁኑ እንጂ በክልል ወይም በጐጥ የተደራጁ ናቸው፡፡ መድረክ ውስጥ ካሉት ስምንት ፓርቲዎች አንድ ፓርቲ ብቻ ነው በአገር አቀፍ ፓርቲነት የሚንቀሳቀሠው ‹‹ዘይትና ውሃን ማዋሃድ ያስቸግራል››፡፡ የተለያየ ርዕዩተ አለም ያለቸውን ፓርቲዎች ለአንድ ዓላማ ማቆም ከባድ ነው፡፡ እንበል ወደሰላማዊ ምርጫ ተመልሶ

ማሸነፍ ቢችል ከአንድነት ( አገራዊ ፓረቲነትን ይዞ ከሚንቀሳቀሰው ) ፓርቲ ውጪ ያሉት ሠባቱ ፓርቲዎች የየራሳቸውን ክልል ይዘው እናስተዳድር ቢሉ አንድነት ምን ሊያሰተዳድር ነው? ነገሩ ገብቶናል፤ በተለያየ ጊዜ ከመድረኩ መግለጫም ሆነ በቅርቡ ከጥምር አመራር ምርጫ በኋላ ከዶ/ር መራራ ጉዲና መረዳት እንደቻልነው ስብስቡን ሊመሠርቱ የቻሉበት ዋነኛው አጀንዳቸው አገርንና ህዝብን እንዴት ማስተዳደር ሳይሆን ገዥውን ፓርቲ በምንም መልኩ ይሁን ከስልጣን ማውረድ ነው፡፡ ይህ የህዝብ ድምፅን ታሳቢ ያላደረገ የጭፍን ጉዞ ደግሞ ውጤቱ የከፋ ሊሆን እንደሚችል የተረዱ አይመስለኝም፡፡

በርዕዬተ ዓለም ፈፅሞ የማይገናኙ ፓርቲዎች ስብስብ ማድረግ ፍፃሜው መበታተን ነው፡፡ መድረክ የሀገራችንን ብሔሮች፤ ብሔረሠቦችና ህዝቦች ይወክላል የሚል እምነት የሚያሳድር ካለ የዋህነት ነው፡፡ መድረኮች በቀጣዩ ምርጫ እንደፓርቲ በምርጫ ተወዳድረን እናሸንፋለን የሚባል እምነት እንደሌላቸውና ይልቁንም በልዩ ልዩ መንገድ መንግስትን በማስገደድ ስልጣን ለመጋራት ማሰባቸውን እየነገሩን ይገኛሉ፡፡ ‹‹በምርጫ ማሸነፍ አንችልም ምክንያቱም ገዥው ፓርቲ አባላቱን እያበራከተ መጥቷል፤ ስለዚህ የግድ የዝምባብዌንና የኬንያን ፈለግ ተከትለን ስልጣን መጋራት አለብን ›› በማለት ወንዝ የማያሻግር ቅስቀሳ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ድርድር ውስጥ ያልገቡትም ይህን ዘዴ ስለዘየዱ ይሆን የሚል ጥያቄ ሳይጭርብኝ አላለፈም፡፡ በጣም ያሳዝናል፡፡

ነገሩ መድረክ ( ጥምረቱ) በቅርቡ ባደረገው የአመራር ምርጫ ላይ ፓርቲውን ለአራት ወራት በሊቀመንበርነት እንዲመሩ የመረጧቸውን ግለሠብ ስሠማ የበለጠ የፓርቲውን የወደፊት ዕቅድ ምን እንደሆነ ይፋ ያረገ ነው የመሰለኝ፡፡ ምንም እንኳ በስብስቡ ውስጥ የሚገኙ አባላት ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ቢሆኑም በአንፃራዊ መልኩ በአስተሣሠብም ሆነ ስርዓት ያለው ንግግር በማድረግ ረገድ ግን ከዶ/ር መረራ የተሻለ ይጠፋል የሚል እምነት የለኝም፡፡ የሊቀመንበርነቱን ቦታ የተሠጣቸው ዶ/ር መራራ በእኔ እይታ “ከፖለቲካ መምህርነታቸው” ባለፈ ለአገራችን ፖለቲካ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ማለት አልችልም፡፡ መድረክ እኝህን በአድርባይነት ፣ በጽንፈኛነትና በጥላቻ ፖለቲካ አራማጅነታቸው የሚታወቁ

ግለሠብ መምረጡ እውነትም ምን አይነት የተሳሳተ መንገድ  እየተጓዘ እንደሆነ ይመለከታል፡፡ ከዚህ በፊትም ቢሆን የሚፈጠሩ ችግሮችን በውይይትና በድርድር ከመፍታት ይልቅ ፍጥጫና ንትርክን የሚመርጡና ነገሮችን ሁሉ በጭፍን ጥላቻ የሚመለከቱት እኚህ ግለሰብ በስብስቡ ውስጥ የሚገኙ አመራሮችን በአንድ ጋሪ እንዲጓዙ በማድረግ ሲጠመዝዙ የሚውሉ እንደሚሆኑ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አይኖርም፡፡

እናም በአሁኑ ጊዜ በአፄዎችና በደረግ ዘመን ያደርጉ እንደነበሩት የይስሙላ ምርጫዎች የሚደረጉበት ሳይሆን ህዝቡ የሚያስተደድረውን ወይም ይበጀኛል ያለውን ሁሉ በነፃነት በድምፅ የሚመርጥበት ጊዜ ነው፡፡ ጊዜው ስልጣን በሀይል ወይም በመፈንቅለ መንግስት የሚይዝበት ሳይሆን በሠላማዊ ምርጫና በሠላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚደረግበት ወቅት ነው፡፡

በመሆኑም የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎችም በውድድር ማሸነፍን ትኩረት በመስጠት አገራችን የጀመረችው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ሊያበረክቱ ይገባል፡፡  ችግሮችን በድርድር መፍታትን ዋነኛ አማራጭ አድርጐ መውሰድ በአገራችን ባህል ሆኖ ሊዳብር ያስፈልጋል፡፡ ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ ለአገሪቱ ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝባችሁ በድርድሩ ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ አገሪቱ የምርጫ ሥነ ምግባር ሕግ እንዲኖራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጋችሁ የገዥውና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በስምምነቱ ላይ ያስቀመጣችሁትን ጠቃሚ ሃሳቦች ወደተግባር እንደምትለውጧቸው ሙሉ እምነት አለኝ፡፡  ድርድሩን ረግጦ የወጣው መድረክ ይህንኑ እንደፖለቲካ ግብ መቁጠሩን አቁሞ ለቀጣይ ድርድር ወደ ሠላማዊው መንገድ ቢመለስ ለራሱም ሆነ ለአገር ይበጃል እላለሁ፡፡